# ሰልባጅ እያመጡ

ከወንጌል ይጠቅሳል ፣ ሰይጣንም አንዳንዴ
ትርፉን የሚያሰላ ፣ የዘውጌ ነጋዴ
ዲሞክራሲ እያለ ፣ ቢሰብክም ለዘዴ
እንክርዳዱን ዘርቶ ፣ እንዴት ይጨድ ስንዴ
ጥበት ያነቀዘው ፣ ያተያይ መደዴ
ድኖ አይድን በሽታ ፣ ያስተሳሰብ ውርዴ ።

ዘመን አይሻገር ፣ ኗሪ ተቸክሎ
ከዘራው እንክርዳድ ፣ አንዷሎ አንዷሎ
ተካልን አቃቤ ፣ ስልቻን ቀንቀሎ
አጓጉል ሸንገላ ፣ የነ ማሞ ቂሎ
ካዳቆነው እምነት ፣ የማይወጣ ችሎ
ከወዴት ይጨደው ፣ ያልዘራውን በቅሎ ።

መች የጠየቀውን ፣ አገኘና ዜጋ
ለጠባቦች ሹመት ፣ ሆኗል አልጋ ባልጋ
አገርን ማን ያውጣት ፣ ከጅቦች መንጋጋ
ሁሌም እንደመሸ ፣ ምሏል ወይ ላይነጋ?
በጥበት ተጠምቃ ፣ የመጣች ተጠርጋ
ፍትሕን ልትገድል ፣ መጣች በር ልትዘጋ ።

መቼ ግድ ሰጥቷቸው ፣ እናቶ ጥጋቤ
ያራሱት ይመስል ፣ እንዳናት ላይ ቅቤ
ሕጉ ሕግ ሊሆን ፣ በአዳነች አቤቤ
በሁለቱም ወገን ፣ የተሳለች ጩቤ
በደንቆሮ ልሂቅ ፣ የተማረች ቁቤ
ከእሳት ወደ ረመጥ ፣ እያወቀው ልቤ ።

ከትላንቱ ዛሬ ፣ ጭራሽ አይን አወጡ
ተምረዋል ስንል ፣ ድንጋይ ሆነው መጡ
እነ ጎጥ አምላኩ ፣ የተሻለ አይሰጡ
ቆንጥሩን አንስተው ፣ አጋም ስላመጡ
እንደተለመደው ፣ ውሃ እየወቀጡ
ምነው የታጋሹን ፣ ቀፎውን ባይንጡ
ጉልቻ ለዋውጠው ፣ ወጥ ላያጣፍጡ
ህዝብ ያሰለቻሉ ፣ ሰልባጅ እያመጡ ።

ታዛቢው

March 13, 2020